ኢኮሥኮ
ECWC

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን
ETHIOPIAN CONSTRUCTION WORKS CORPORATION

# የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን
# የስራ ቦታዎች ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና እና የኤድስ
# ፈንድ መቆጣጠሪያ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 012/2011

**ሰኔ 2011 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

## ማውጫ


**መግቢያ**..........1

ክፍል አንድ..........2

ጠቅላላ..........2

1. አጭር ርዕስ..........2

2. ትርጓሜ..........2

3. ዓላማ..........4

4. የተፈፃሚነት ወሰን..........4

ክፍል ሁለት..........5

ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለሚከናወኑ ተግባራት እና ኃላፊነቶች..........5

5. **በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት**..........5

6. የኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሚናና ኃላፊነት..........6

7. የሠራተኞች ሚናና ኃላፊነት..........8

8. የኤች.አይ. ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸዉ ሠራተኞች ሚናና ሀላፊነት..........8

9. የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል መቋቋም..........9

10. የፀረ ኤችአይ ቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል አባላት አሰያየም..........9

11. ስለ ግብረ ኃይሉ የስራ ዘመን..........10

12. የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል ሚናና ኃላፊነት..........10

13. የግብረ ሃይሉ ሰብሳቢ ሚናና ሃላፊነት..........11

14. የግብረ ሃይሉ ም/ሰብሳቢ ሚናና ሃላፊነት..........11

15. የግብረ ሃይሉ የሂሳብ/ክፍያ ባለሙያ ሚናና ሀላፊነት..........11

16. የኤችአይ ቪ ኤድስ ሜንስትሪሚንግ ባለሙያ/ ፎካል ፐርሰን ሚናና ሃላፊነት..........12

17. ስለ ግብረ- ኃይሉ ስብሰባዎችና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት..........13

18. ኦዲትን በተመለከተ..........14

19. የሠራተኞች መብት..........14

20. ስለ ዝውውር..........15

ክፍል ሶስት..........16

ስለ ፀረ ኤችአይ ቪ/ኤድስ ፈንድ መቋቋም፣ ድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ..........16

**21.** ስለ ፀረኤችአይ ቪ/ኤድስ ፈንድ መቋቋም..........16

22. ስለ ፀረኤችአይ ቪ/ኤድስ ፈንድ ምንጮች..........16

23. ፈንድን ስለማስተዳደር..........16

24. ስለ ፈንድ አጠቃቀም..........16

**25.** ስለ ድጋፍና እንክብካቤ....17
26. ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ሰራተኞች ....17
27. ድጋፍና እንክብካቤ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች....17
28. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ....19
29. የኤድስ ፈንድ ዝውውርን በተመለከተ ....20
30. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ ስለማሳወቅ....21
31. የድጋፍና እንክብካቤ ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች....21
32. ከኤች አይ ቪ ኤድስ ጋር የተያያዙ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ....22
33. ስለ ዲሲፕሊን ክስ አቀራረብና ስለ ውሳኔ አሰጣጥ....23
34. ስለ ዲሲፕሊን ቅጣት ....23
35. ከመመሪያው ጋር የሚቃረኑ ሕጎችና አሰራሮች ....23
36. መመሪያውን ስለማሻሻል ....24
**37.** መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ....24

# መግቢያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና የጤና ችግሮች በስፋት ይስተዋላሉ፡፡ የዜጎች የኢኮኖሚ ችግር ለተለያዩ የማህበራዊ ችግሮች በተለይም ለበርካታ አይነት የጤና ችግር እንደሚያጋልጥ የሚታወቅ ቢሆንም የሰዎች ህይወትን በሃላፊነት አለመምራት፣ የግንዛቤ እጥረቶችና መሰል ችግሮችም ለበርካታ ዓይነት የጤና እክሎች ያጋልጣሉ፡፡ሀገራችንን ከድህነት ለማላቀቅ እና የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ የሚቻለው መሰልማህበራዊ ችግሮችን በጋራ መቅረፍ ሲቻል እንደሆነ ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ ኮንሥትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በሀገሪቱ የሚከናወኑ ግዙፍ ግንባታዎች ላይ እየተሳተፈ የሚገኝ ሲሆን በምንም የማይተካ ሚና የሚጫወተውን የሰው ሀይል የሚያሳጣ በሽታ አሳሳቢ የስራ ቦታዎች የልማት ችግር መሆኑን በመገንዘብ በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና መሰል ችግሮችም ክንያት ለኤች.አይ .ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የመ/ቤቱ ሰራተኞች ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሰጥበትን ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑይህ የሥራ ቦታዎች ኤች.አይቪ/ኤድስ መከላከያ መቆጣጠሪያ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ የሥራ ቦታዎች የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ የአፈጻጸም መመርያ የተዘጋጀው በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት፣ ፕሮጀክቶችና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ላይ የሚገኙ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞችን እንዲሁም የሰራተኞችን ልጆች ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡በኮርፖሬሽኑ ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች ከኤችአይ ቪ ወረርሽኝ ለመከላከል ኤችአይ ቪ በደማቸው ውስጥ ያለ ህሙማን ሰራተኞች ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸው ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆ ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ማስቻል ወሳኝ መሆኑን በመረዳት ይህን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የስራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ እና የኤድስ ፈንድ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 024/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. **"ኮርፖሬሽን"**ማለት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ነው፡፡

2.2. **"ኤችአይ ቪ"** ማለት ሰውነት በተፈጥሮ በሽታን ለመቋቋምና ለመካለከል ያለውን ችሎታ ወይም ብቃት የሚሸረሽርና ደረጃ በደረጃ ለበሽታ ወይም ለኢንፌክሽን የሚዳርግ ቫይረስ ነው፡፡

2.3. **"ኤድስ"** ማለት በኤች አይቪ ሳቢያ ሰውነት በተፈጥሮ ያለውን በሽታ የመከላከል ችሎታ በማዳከም በተለያዩ ተዛማጅ ሕመሞች ከተያዘ በኋላ የሚከሰት የበሽታ መገለጫ ነው፡፡

2.4. **"ኤች አይቪ/ኤድስ በደሙ ውስጥ የሚገኝሰው"** ማለት አግባብ ካለው ባለስልጣን ፈቃድ ባገኘ የጤና ተቋም የግለሰቡ የደም ናሙና ተወስዶ ደረጃውን በጠበቀ ምርመራ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ ስለመኖሩ የፅሁፍ ማስረጃ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.5. **"አብይ ኮሚቴ"** ማለት በዋናዉ መ/ቤት የሚቋቋም የኤ.ች.አይ.ቪ. መከ/መቆ/ኮሚቴ ነዉ፤

2.6. **"ንዑስ ኮሚቴ" ማለት** በቅርንጫፎች እና በፕሮጀቶክች የሚቋቋም የኤች.አይ./ቪ. መከ/መቆ ኮሚቴ ማለት ነዉ፤

2.7. **"በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ. የተጐዳ ቤተሰብ"** ማለት ኤች.አይ ቪ.ቫይረስ በደሙ መኖሩ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ሰራተኛ እና በኤድስ ሳቢያ በሞት መለየቱ የተረጋገጠ የመ/ቤቱ ባልደረባ ከ18 አመት በታች የሆኑ ልጆች ናቸው፤

2.8. **"የኮርፖሬሽኑ ሰራተኛ"** ማለት በኮርፖሬሽኑ ውስጥ በኮንትራትና ቋሚ ሰራተኝነት ተቀጥሮ የሚሰራ የስራ መሪና ሰራተኛ ነው፡፡

2.9. **"ኤች.አይ.ቪ ሜይንስትሪሚንግ"** ማለትበየደረጃው በሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ተቋማት የኤችአይቪ፣ኤድስ ወረርሽኝን ለመከለከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ ቀጣይነትና ውጤታማ ባለው ሁኔታ የወረርሽኙን ስርጭትና ተፅዕኖ ለመቀነስና ለመቀልበስ የዋናው መደበኛ ሥራ አካል በማድረግ የሚተገበርነው፡፡

2.10. **"የኤች.አይ.ቪ /ኤድስ. ሜይንስትሪሚንግ ግብረኃይል"** ማለት በኮርፖሬሽኑ በማናቸውም ደረጃ በተቋቋመ መስሪያ ቤት ውስጥ በስራ ቦታ የኤች. አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የመሪነቱን ሚና የሚጫወት አካል ነው፡፡

2.11. **"የስራቦታ"** ማለት የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች ሥራቸውን የሚያከናውኑበት መደበኛ ሥፍራ ሲሆን በመስክ የሥራ ማከናወኛ ሥፍራንም ይጨምራል፡፡

2.12. **"ድጋፍና እንክብካቤ"** ማለት ኤች.አይ. ቪ. ኤድስ በደማቸው ውስጥ ላለና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች ሥራቸውንና ቀጣይ ሕይወታቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲመሩና የቫይረሱን ስርጭት በመቀነስ ረገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያግዝ ሰብዓዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግባር ነው፡፡

2.13. **"ምስጢር /Confidentiality/"** ማለት አንድ ሰው የምርመራ ውጤቱ የህመሙ ሁኔታ ከኤች.አይ.ቪ.. ኤድስ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመለክተው የህክምና ሁኔታ ወይም በድጋፍና እንክብካቤ መካተቱን/ ዋን ማወቅ ከሚገባቸው ባለሙያዎች እና ከሠራተኛው/ዋ ውጪ በግልጽ በየማይወጣበት ሥርዓት ነው፡፡

2.14. **"የመከላከል ተግባር"** ማለት የኤች.አይ. ቪ. ኤድስ በደሙ ውስጥ ከሚገኝበት አንድ ሰው ወደ ጤነኛው ሰው እንዳይዛመት የሚረዳ ማንኛውም የማስተማርና ሌሎች ተግባሮችን ያካትታል፡፡

2.15. **"መቆጣጠር"** ማለት የኤች. አይ. ቪ. ቫይረስን ሥርጭት እና ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳይ ባለበት ለማቆም የሚወሰድ የመከላከል ተግባር ክትትልና እርምጃ ነው፡፡

2.16. **"ምቹ የሥራ ሁኔታ"** ማለት የሥራ ላይ ህመም፣ የሥራ ላይ ጉዳት የጾታ ትንኮሣ፣ ቫይረሱ በደማቸው ውሰጥ የሚገኝ ሰዎችን ጤና፣ እና ሞራል ከሚነኩ የማግለልና አድሎዓዊ ድርጊቶች የፀዳ የሥራ ሁኔታን የሚያጠቃል ልነው፡፡

2.17. **"መረጃ ማለት"** ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ አስመልክቶ በሁሉም ዘንድ በግልጽ ሊታወቅ የሚገባው አህዛዊ ጥንቅር ወይም ንድፈ ሀሳባዊ ንጽጽርና ትንታኔ የያዘ ወቅታዊ ሰነድ ነው፡፡

2.18. **"ፎካል ፐርሰን"** ማለት በዋና መ/ቤት፣ በቅርንጫፍ እና ፕሮጀክቶች የኤች አይቪን ስራዎች የሚሰራ ባለሙያ ነው፡፡

2.19. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተጠቀሰው ሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመርያ ዓላማ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ኤ.ች አ.ይ ቪ ኤድስን ለመከላከል ፣ለመቆጣጠር የድጋፍና እንክብካቤ ስራዎችን በማስመልከት የሚነደፉትን ፕሮግራሞች የህግ ማዕቀፍ በመስጠት በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት ዘርፎች፣ፕሮጀክቶችና ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለሚከናወኑ ተግባራት እና ኃላፊነቶች

5. **በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት**

5.1. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታዎችና አጠቃላይ አገራዊ የልማት ችግሮች መሆኑን በመቀበል ወረርሽኙ በኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ አፈፃፀምና በሠራተኞች ኑሮ ላይ የሚያስከትለውን ዘርፈ-ብዙ ተፅዕኖ ለመቋቋም በባለቤትነት ስሜትና በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ፡፡

5.2. የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን በመንደፍና በመተግበር የኮርፖሬሽኑ የሥራ ቦታዎች ከኤች.አይ. ቪ/ኤድስ የፀዱ ምቹና ጤናማ እንዲሆኑ ማድረግ ፣

5.3. በኮርፖሬሽኑ የሥራ ቦታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ፣ሠራተኞችንና ሌሎች ተባባሪ አጋር አካላትን ያቀፈ ዘላቂ ተቋማዊ አደረጃጀት ያለው በዕቅድና በበጀት የሚመራ ፣ ግልፅ አሳታፊና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር መፍጠር፣

5.4. የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያን አቅም በማጎልበት አጠቃላይ የኤች.አይ.ቪ. መከላከለያ፣ መቆጣጠሪያና የድጋፍና እንክብካቤ ስራዎችን ባለቤት በማድረግ ስራዎችን እንዲያከናውን ማስቻል፣

5.5. የኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ፣ የአባላዘር በሽታዎችንና ሌሎች ተጓዳኝ በሽታዎችን የሚመለከት ወቅታዊ መረጃ ማቅረብ እንዲሁም የመከላከልና የመቆጣጠሩን አጠቃላይ ፕሮግራም ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት፣

5.6. በኮርፖሬሽኑ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ፣ የአባላዘር በሽታዎችንና ሌሎች ተዛማጅ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚነደፍ ማንኛውንም ፕሮግራም በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መርህ ላይ የተመሠረተ የሴቶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት የሚያጎለበት ማድረግ፣

5.7. በተፈጥሮአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ለኤች.አይ.ቪ. ስርጭት ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ አካል ጉዳተኛ ሰራተኞች ልዩ ትኩረት መስጠት፣

5.8. አጠቃላይ ሰራተኛው ስለ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ አለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያገኙ ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርት እንዲሰጥ ማድረግ፤

5.9. በሥራ ላይ ያሉ ሠራተኞች እና በኮርፖሬሽኑ ለመቀጠር የሚቀርቡ ሥራ ፈላጊ አመልካቾች የኤች.አይ. ቪ. ምርመራ እንዲያደርጉ አለማስገደድ፤

5.10. የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ. ቪ. ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታት ፤የምርመራ ውጤቱም ሰራተኛው እንዲታወቅ ካልፈቀደ በስተቀር በምስጢር ጠብቆ መያዝ፤

5.11.ኤች.አይ. ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞችና ሥራ ፈላጊ አመልካቾች ላይ ምንም አይነት መድልዎና መገለል አለማድረግ፤

5.12. ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ሰራተኛ በደሙ ውስጥ በመኖሩ ወይም የኤድስ ህመምተኛ በመሆኑ ምክንያት ብቻ የሥራ ውሉ እንዲቋረጥ ያለማድረግ፤

5.13. ኤች.አይ. ቪ. በደማቸው ውስጥ ላለና ኤድስ ህሙማን ለሆኑ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች በጀት በመያዝ አስፈላጊውን ድጋፍና ክብካቤ ማድረግ

5.14. በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት፣ ዘርፎች፣ ቅርንጫፎች ፤ ፕሮጀክቶች እናሳይቶች ላይ በሚሰሩ ሴት ሰራተኞች ላይ ፆታዊ ጥቃት እንዳይደርስባቸውና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤

5.15. በኮርፖሬሽኑ ሁሉም ፕሮጀክቶችና ቅርንጫፎች ላይ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር እንዲያስችል ለሥራው በጀት ይዘው ሥራዎችን እንዲሰሩ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

5.16. በኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶችና ቅ//ቤቶች የሚመለከታቸው ባለሙያዎች እየተዘዋወሩ ስለ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር የሚሰሩ ስራዎችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን መስጠት፤

## 6. የኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሚናና ኃላፊነት

የኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ (የዘርፎች፣ቅ/ፅ/ቤቶችና ፕሮጀክት ሀላፊዎች) የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

6.1. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ የሥራ ቦታዎች የልማትና ሊሰጥ ስለሚገባው የተቀላጠፈ አገልግሎት አሰጣጥ ዋናችግር መሆኑን በመገንዘብ ወረርሽኙን ለመግታትና የኮርፖሬሽኑተልዕኮ አፈጻጸም እንዲሁም በሰራተኞች ኑሮ ላይ የሚያስከትለውን ዘርፈብዙ ተፅዕኖ ለመቋቋም ግንባር ቀደም በመሆን ቁርጠኝነት የተሞላበት አመራር መስጠት፤

6.2. በብሔራዊ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ በመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሥራ ቦታዎች የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ህጎችና በዚህ መመሪያ መሠረት የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚደረጉትን ሥራዎች በበላይነት መቆጣጠር፤

6.3. በኮርፖሬሽኑ የሥራ ቦታዎች ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚነደፉ እቅዶችና ፕሮግራሞች የሥራዓተ-ጾታ እኩልነትንና ልዩ ትኩረት የሚሹ ሠራተኞችን ያገናዘበ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

6.4. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተነደፉ እቅዶችና ፕሮግራሞች ከዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈጻጸም የሚኖራቸው አጠቃላ ይሂደት ግልጽነት /አሳታፊነት ፤ ፍትሐዊነትና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

6.5. የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ፈንድ ማቋቋም ፤ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን መከታተል፤

6.6. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን ሠራተኞች በሥራ ቦታዎች ሰብአዊ መብታቸው የተከበረ መሆኑን ፤ ተገቢው ድጋፍና ክብካቤ መደረጉን ማረጋገጥ፤

6.7. ኤች.አይ. ቪ በደማቸው ውስጥ ካለና ከኤድስ ህሙማን ሰብአዊ መብት አጠባበቅ ድጋፍና ክብካቤ በአጠቃ ላይ ከፀረ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ጥቆማዎች ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ተቀብሎ ውሳኔ መስጠት፤

6.8. የፀረኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ኮሚቴ/ግብረ ኃይል ማቋቋም

6.9. የፀረኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ባለሞያ መመደብ

6.10. የፈንዱን የወጪና የገቢ አጠቃቀም የኦዲት ምርመራ የሚያደርጉ ሶስት አባላት መመደብ፤

6.11. በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት፣ ዘርፎች፤ ቅርንጫፎችና ፕሮጀክቶች ላይ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እቅድና በጀት መያዙን መከታተልና ውሳኔ መስጠት፤

## 7. የሠራተኞች ሚናና ኃላፊነት

ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

7.1. ለአባላዘር ኢንፌክሽንና ለኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች ራሱን በመጠበቅ ለሌሎች መልካም አርአያ መሆን፤

7.2. ኮርፖሬሽኑ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና መቆጣጠር ለሚነድፋቸው ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ተግባራዊነት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ፤

7.3. በሥራ ቦታዎች ወሲባዊ ድርጊት ከመፈፀም መታቀብ፤

7.4. በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ዙሪያየ ሚሰጡ ሥልጠናዎችን ፤ ምክሮችንና ወቅታዊ መረጃዎችን በንቃት የመከታተልና ተግባራዊ ማድረግ፤

7.5. ኮርፖሬሽኑ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚዘረጋቸው አሠራሮች ላይ በንቃት መሳተፍ፤

7.6. ኤች.አይ. ቪ. በደማቸው ውስጥ በሚገኝ ኤድስ ህሙማን ሠራተኞች በውሳኔ አሠጣጥ፣ በሥራ ግንኙነት ፤ በቃላት፤ በድርጊት ወይም በሌሎች ዘዴዎች አድሎና መድሎ ከመፈጸም በመቆጠብ ሰብአዊ መብታቸውን ማክበር፤

7.7. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚካሄደውን ጥረት ለማሳካት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሙያ፤ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፤

7.8. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ይህን መመሪያ ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፤

## 8. የኤች.አይ. ቪ. ቫይረስ በደማቸው ውስጥ የተገኘባቸዉ ሠራተኞች ሚናና ሀላፊነት

ቫይረሱ በደሙ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሠራተኛ የሚከተሉትን ተግባራትና ኃላፊነቶች የመፈፀም ግዴታ አለበት፤

8.1. ለአባላዘር ፤ኤች.አይ. ቪ/ኤድስና ለተጓዳኝ በሽታዎች የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት በአግባቡ በመከታተልና ህመሙን ከሚያባብሱ ደባል ሱሶች በመታቀብ ጤንነቱን የመጠበቅ ለኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ ማበርከት፤

8.2. ራሱን ከማግለል ተቆጥቦ ተገቢውን የሥራና የማህበራዊ ግንኙነት ማጎልበት

8.3. ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ኤች.አይ. ቪን ወደ ሌላ ላለማስተላለፍ ጥንቃቄ በማድረግ ሠራተኞችንና መላውን ህብረተሰብ ከወረርሽኙ ስርጭት ለመጠበቅ ያለበትን ኃላፊነት በተነሳሽነትና በተቆርቋሪነት ስሜት መወጣት፤

8.4. እንደ ማንኛውም ሠራተኛ አግባብ ያለውን ሕግ ፣ደንብና መመሪያ በማክበር የመስራት፤

8.5. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ያለውን ተሞክሮ በፍቃደኝነት ለሠራተኞች በማጋራት አርአያ መሆን፤

## 9. የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል መቋቋም

የኤችአይ ቪ/ ኤድስ መከላከያ፣ መቆጣጠሪያና ድጋፍና እንክብካቤ ስራውን የሚያስተባብር የፀረ ኤች.አይ ቪ ግብረሃይል በዋና መ/ቤት፣ ዘርፎች፣ ፕሮጀክቶችና ቅርንጫፎች በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

## 10. የፀረ ኤችአይ ቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል አባላት አሰያየም

የፀረ ኤች አይ ቪ ግብረኃይል አባላት ብዛት ሰባት ሆኖ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት ቁጥሩ ሊበልጥ ወይም ሊያንስ ይችላል፡፡

10.1. በዋና መ/ቤት የሚቋቋመው ግብረሀይል ተጠሪነቱ ለዋና ስራአስፈጻሚ ይሆናል፡፡

የፀረኤች አይ ቪ ግብረኃይል በኮርፖሬሽኑዋና መ/ቤት የሚከተሉትን አባላት ያካትታል፡፡

- በኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሚሰየም ኃላፊ.................................ሰብሳቢ
- በኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሚሰየም ኃላፊ..............................ም/ሰብሳቢ
- የኮርፖሬሽኑ የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ.................................አባል
- በኮርፖሬሽኑ በሚደረግ የህፃናት ድጋፍ የእናት አምባሳደር ተወካይ......... አባል
- የኮርፖሬሽኑ የሰራተኛ ማህበር ተወካይ............................................ አባል
- የኮርፖሬሽኑ የሂሳብ እና ክፍያ ባለሙያ ............................................ አባል
- የኮርፖሬሽኑ የኤችአይ ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ባለሙያ............አባልና ጸሃፊ

10.2. በቅርንጫፍ እና ፕሮጀክቶች የሚቋቋመው ግብረ ሀይል ተጠሪነቱ ለቅርንጫፉ ወይም ለፕሮጀክቱ ሀላፊ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

- የቅርንጫፍ /ፕሮጀክቱ ሰው ሀብት አስተዳደር ቡድን..............................ሰብሳቢ
- ቅርንጫፍ/ፕሮጀክቱ የሰራተኛ ማህበር ተወካይ....................................አባል
- ❖ የቅርንጫፍ/ፕሮጀክቱ የሂሳብእና ክፍያ ባለሙያ.................................... አባል ቅርንጫፍ/ፕሮጀክቱ በሚደረግ የህፃናት ድጋፍ የእናት አምባሳደርነት ተወካይ…አባል

- የፕሮጀክቱ የኤችአይ ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ባለሙያ........አባልና ፀሃፊ የቅርንጫፍና ፕሮጀክት ሰብሳቢው በማይኖር ጊዜ የቅርንጫፍ ወይም የፕሮጀክቱ የሰራተኞች ተወካይ ስብሰባውን ይመራል፡፡

## 11. ስለ ግብረ ኃይሉ የስራ ዘመን

የግብረኃይሉ አባላት የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አባሉ ለተጨማሪ ሁለት አመታት ሊመረጥ ይችላል፡፡

ይህ የስራ ዘመን በዋና መ/ቤት በተቋቋመው ግብረሀይል የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያን እና ኤች.አይ.ቪ. ሜንስትሪሚንግ ባለሙያን አይመለከትም፡፡እንዲሁም በዲስትሪክትና ፕሮጀክት ላለው ግብረሀይል የሰው ሀብት አስተዳደር ቡድን እና ኤች አይ ቪ. ሜንስትሪሚንግ ባለሙያን አይጨምርም፡፡

## 12. የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል ሚናና ኃላፊነት

የፀረ ኤች አይ ቪ. ግብረ ኃይል ተጠሪነቱ ለኮርፖሬሽኑ/ቅርንጫፍ/ፕሮጀክት የበላይ ሃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

12.1. የብሄራዊ ኤችአይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ የሥራ ቦታዎች ኤችአይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ፣ ኤችአይ ቪ. ኤድስን የሚመለከቱ ሌሎች የፌደራል መንግስት ህጎችና ይህ መመሪያ በኮርፖሬሽኑ ውስጥ እንደየአግባቡ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

12.2. የስራ መርሃ ግብር እና አመታዊ ረቂቅ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

12.3. በኮርፖሬሽኑ የሥራ ቦታዎች ኤች.አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ የሙያ፣ የቴክኒክ፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ እገዛ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

12.4. የኤችአይ ቪ. ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለ እና የኤድስ ህሙማን ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ወይም አገልግሎት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ በሚቀርብ ብህሳብ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

12.5. የፀረኤችአይ ቪ. ፈንድ የሚመራ በትን የፋይናንስ ስርዓት ያወጣል፣በስርዓቱ መሰረት ፈንዱን ያስተዳድራል፡፡

12.6. የኤች አይ ቪ ፈንድ ስለሚዳብርበት ሁኔታ በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ያደርጋል፡፡

12.7. ፅህፈት ቤቱ የሚመራበትን የአሰራር ስርዓት ያዘጋጃል፤ በኮርፖሬሽኑ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

12.8. በኮርፖሬሽኑ የበላይ ሀላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 13. የግብረ ሃይሉ ሰብሳቢ ሚናና ሃላፊነት

የፀረ ኤች አይ ቪ ግብረ ኃይል ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

13.1. የግብረሃይሉን ቋሚና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይመራል፤

13.2. የፈንዱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይከታተላል ከግብረ ሃይሉ ጋር በጋራ ይወስናል፤

13.3. ከግብረ ሃይሉ በሚቀርበው ሃሳብ መሰረት ኮርፖሬሽኑ ፈንዱን የሚደግፍበትን ሃሳቦች ግብረ ሃይሉን በመወከል ያቀርባል፤

13.4. የግብረ ሃይሉን ድጋፍ አስመልክቶ አግባብ ያላቸው ሰነዶችን/ቼኮች/ ላይ ይፈርማል፡፡

## 14. የግብረ ሃይሉ ም/ሰብሳቢ ሚናና ሃላፊነት

የፀረ ኤች አይ ቪ ግብረ ኃይል ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

14.1. የግብረ ሃይሉ ሰብሳቢ በማይኖር ጊዜ ስብሰባዎችን ይመራል፤

## 15. የግብረ ሃይሉ የሂሳብ/ክፍያ ባለሙያ ሚናና ሀላፊነት

15.1. በግብረ ሃይሉ የሚንቀሳቀሰውን ፈንድ ወጪና ገቢን ይቆጣጠራል፤

15.2. የፈንድ ማንቀሳቀሻና ሰነዶችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤

15.3. የግብረ ሃይሉን የሂሳብ ስራዎች ይከታተላል፤ያማክራል፤

15.4. የባንክ ባላንስ (bank balace statement) ተከታትሎ በማምጣት የማስታረቅ ስራዎችን ያከናውናል፤

15.4. የሂሳብ ሰነዶችን (ቼክና የመሳሰሉትን) ይይዛል፤ያዘጋጃል

## 16. የኤችአይ ቪ ኤድስ ሜንስትሪሚንግ ባለሙያ/ ፎካል ፐርሰን ሚናና ሃላፊነት

የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የኤች.አይ. ቪ.ና ተዛማጅ በሽታዎች ፎካል ፐርሰን ወይም የፕሮጀክት የፀረኤች.አይ. ቪ. ፎካል ፐርሰን የሚከተሉት ሚናና ሃላፊነት ይኖሩታል፡-

16.1. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተለያዩየ ሥራ ሂደቶች የሚነደፉትን ፕሮግራሞችና እቅዶች ያቀናጃል፤ የሚደረጉ ጥረቶችን ያስተባብራል፤

16.2. በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚወጡ ወቅታዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በማጠናከርና በማሰራጨት ሠራተኞች እንዲያውቋቸው ያደርጋል፤

16.3. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ በኮርፖሬሽኑ እያደረሰ ያለውን ተፅዕኖ እያጠና ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለግብረ-ኃይሉ ሃሳብ ያቀርባል፤

16.4. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ሥልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እያቀናጀ ተግባራዊ ያደርጋል፤

16.5. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን በተመለከተ የሚሰጡ ትምህርትና ስልጠናዎች በተለይ ለበሽታ ተጋላጭ የሆኑትን ሴት ሰራተኞችና የአካል ጉዳተኞችን ያገናዘበ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

16.6. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለሚወጡ ዕቅዶች ማስፈፀሚያ የሚውል የሃብት ምንጭ የሚገኝበት መንገድ ያፈላልጋል፤

16.7. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ህጎችንና መመሪያዎችን የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች እንዲያውቋቸው ያደርጋል፡፡ መተግበራቸውንም ይከታተላል፣ ይገመግማል

16.8. በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ዙሪያ ከሚሰሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሌሎች አካላት ጋር በአጋርነት ይሠራል፤

16.9. በዘርፍ/በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች /በፕሮጀክት የፀረኤች.አይ. ቪ. ፎካል ፐርሰን የተቋቋሙትን የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ግብረ-ኃይል ይከታተላል ያስተባብራል ፤ይገመግማል፤ የሥልጠና ሥርአቶችን እያቀናጀ ተግባራዊ ያደርጋል፤

16.10. በኤች.አይ. ቪ. ቫይረስ በደማቸው የሚገኝ ሠራተኞች ሚስጥራቸውን በመጠበቅ ክትትል ያደርጋል፤

16.11. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን አፈፃፀም በተመለከተ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ለኮርፖሬሽኑ ሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መመሪያ ሪፖርት ያቀርባል በዋና መ/ቤት ያለውፎካል ፐርሰን ሪፖርቶችን በማጠናቀር ለኮርፖሬሽኑ ስትራቴጂክ ማኔጅመንትና ፕላኒንግ መምሪያ ወርሃዊ ሪፖርት ያቀርባል፤

16.12. ድጋፍ ስለሚያስፈልጋቸው የኤድስ ህሙማን እያጠናከረ ግብረኃይሉ ጋር ውሳኔ እንዲሠጥበት ያደርጋል ፤

16.13. ኤች.አይ. ቪ. ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች ገንዘብ ነክ ከሆኑ ድጋፎች ውጭ የድጋፍ አገልግሎት ሲጠይቁ ምስጢር በኤች.አይ.ቪ. እና ተዛማጅ በሽታዎች ፎካል ፐርሰን ብቻ ተይዞ በተለያዩ የሥራ ቦታ ላይ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

16.14. ከኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ግብረ-ኃይል ጋር ተቀናጅቶ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮችንም ያከናውናል፤

16.15. የግብረ-ኃይሉ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል

## 17. ስለ ግብረ- ኃይሉ ስብሰባዎችና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት

17.1. የፀረኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ግብረ-ኃይል ቢያንስ በወር አንድ ግዜ መደበኛ ስብሰባይ ኖረዋል፣ ሆኖም አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የኮርፖሬሽኑ/ቅርንጫፍ /ፕሮጀክቱ የፀረኤች.አይ. ቪ.ፎካል ፐርሰን በሚያቀርበው ጥሪት በማንኛውም ግዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

17.2. ግብረ-ኃይሉ በዚህ መመሪያ በተሰጠው ሃላፊነት መሠረት ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ ስምምነት ውሳኔ ያስተላልፋል፤ ሆኖም በአባላቱ መካከል የሃሳብ ልዩነት ሲያጋጥም በአብላጫ ድምፅ ይወስናል፤ የተሰጠው ድምፅ እኩል በእኩል ሲሆን በሴቶችና

ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የኤች.አይ. ቪና ተዛማጅ በሽታዎች ኤክስፐርት/ በዲስትሪክት/ ፕሮጀክቶች ፎካል ፐርሰን እና በሰብሳቢው የተደገፈ ሃሳብ ተፈፃሚ ይሆናል፤

## 18. ኦዲትን በተመለከተ

የጸረ ኤችአይ ቪ ኤድስ ፈንድ ኦዲትን በተመለከተ የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

18.1. የፀረኤ.ች.አይ.ቪ. ግብረ-ኃይሉ የሥራ አፈጻጸም በየ3 ወሩ ይገመግማል ፤የአሰራር ግድፈቶች ሲኖሩ የመፍትሄ እና የአሰራር ማሻሻያ/ማስተካከያ/ ሃሳቦችን ይቀርባል፤

18.2. የፈንዱን የገቢና የወጪ ሂሳቦችን ይመረመራል፤

18.3. በየ6 ወሩ ስለኮሚቴው የፋይናንስና ሥራ አፈጻጸም እንቅስቃሴ ለማኔጅመን ትሪፖርት ይቀርባል፤

18.4. ለግብረ-ኃይሉ ጠቃሚ የሆኑ የሂሳብ እና የንብረት አያያዝ ስልቶችን ይቀየሳል፤

## 19. የሠራተኞች መብት

19.1. የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ባለሞያ ቅርንጫፍ /ፕሮጀክት ኤችአይ ቪ ፎካል ፐርሰን እና ግብረ-ኃይል በሚነድፏቸው ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በሚሠጧቸው አገልግሎቶች እኩል ተሳታፊ መሆን፡፡

19.2. የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ባለሞያ የቅርንጫፍ /ፕሮጀክቱ የፀረኤች.አይ.ቪ. ፎካል ፐርሰን እናግብረ-ኃይሉ በሚያዘጋጇቸው የምክክር ስብሰባዎች፤ሥልጠናዎችና ፕሮግራሞች ላይ የመካፈል፤

19.3. የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ እና ግብረ-ኃይሉን አጠቃላይ አሠራር ወይም የኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ፈንድ አጠቃቀም ግልፅ እንዲሆን ላቸው የመጠየቅ ማብራሪያ የማግኘትና የማወቅ፤

19.4. በፆታ፤በአካል ጉዳት፤ በኢኮኖሚ ወይም በማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ከኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ተጋላጭነት ጋር በተያያዘ የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥመው ይህንኑ በማስረዳት ልዩ ድጋፍ የመጠየቅ፤

19.5. ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን በተመለከተ ሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ እና ግብረኃይሉን ይዞታ ሥር የሚገኙ መረጃዎችን ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ የማግኘት፤

19.6. በመምሪያው እና ግብረ-ኃይሉ አሠራርና በፀረ ኤች.አይ. ቪ /ኤድስ እንቅስቃሴ የአፈጻጸም ሂደት ቅር ሲሰኝ አቤቱታ የማቅረብና የመደመጥ፤

19.7. ማንኛውም ሠራተኛ በሙሉ ነፃ ፈቃደኝነት የኤች፤አይ. ቪ/ኤድ ምርመራ እንዲያደርግ ይበረታታል ሆኖም የምርመራውን ውጤት ይፋ እንዲያደርግ አለመገደድ፤

19.8. የኤች.አይ. ቪ. የምርመራ ውጤትና መረጃዎች ጥብቅ ሚስጢር ሆነው ይያዛሉ፤ይፋ ሊደረጉ የሚችሉት ተመርምሮ ውጤቱን ባቀረበው ሠራተኛ ነፃ ፈቃድና የጽሁፍ ስምምነት ብቻ ይሆናል፡፡

19.9. ኤች.አይ. ቪ. ቫይረስ በደም ውስጥ ቢኖርም በትምህርት እና ሥልጠና፣ በደረጃ እድገት፣ በድልድል፣ በምደባበ ጊዜ አድሎ ሳይደረግበት ተሳታፊ እና ተጠቃሚ መሆን፤

## 20. ስለ ዝውውር

20.1. የኤድስ ህመምተኞች የሆኑ ማንኛቸውም የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች የተመደቡበትን የሥራ መደብ ተግባርና ኃላፊነት በሚገባ ለመፈፀም የመሥራት አቅማቸው ሲደክም የያዙት ደመወዝ ሳይቀነስባቸው በራሳቸው ስምምነት አቅማቸው ወደሚፈቅድላቸው የሥራ መደብ ተዛውረው እንዲሰሩ የሚቻለውን ጥረት ይደረጋል፡፡

20.2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(1) በተጠቀሰው ምክንያትም ሆነ አግባብነት ባላቸው የፌደራል መንግስት ሠራተኞች ህጎች መሰረት ዝውውር ሲፈፀም ኤች.አይ. ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለ ሠራተኞችን ለተጓዳኝ በሽታዎች በሚያጋልጡ የሥራ ቦታዎች ላይ አዛውሮ

ማሰራት የተከለከለ ነው፡፡ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም ሲባል የሚዛወሩበት የሥራ ቦታ ለተጓዳኝ በሽታዎች የማያጋልጥ መሆኑ ከዝውውሩ በፊት መረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ ፀረ ኤችአይ ቪ/ኤድስ ፈንድ መቋቋም፣ ድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ

### 21. ስለ ፀረኤችአይ ቪ/ኤድስ ፈንድ መቋቋም

የኢትዮጵያ ኮንሥትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፈንድ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

### 22. ስለ ፀረኤችአይ ቪ/ኤድስ ፈንድ ምንጮች

የፀረኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፈንድ የገቢ ምንጭ ከሰራተኛው ከሚሰበሰብ መዋጮ፣ ከኮርፖሬሽኑ ከሚገኝ ድጋፎችና ከተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ከሚገኝ ገንዘብ ይሆናል፡፡

22.1. ከሰራተኛው የሚሰበሰብ ገቢ ከእያንዳንዱ ቋሚና ኮንትራት ሰራተኛ 0.5% ይሆናል፡፡

22.2. ኮርፖሬሽኑ በየዓመቱ በጀት በመያዝ ፈንዱን ይደግፋል፡፡

### 23. ፈንድን ስለማስተዳደር

የፀረኤችአይ ቪ ፈንድ የሚያስተዳድረው በዚህ መመሪያ የተቋቋመው ግብረ ኃይል ነው፡፡

### 24. ስለ ፈንድ አጠቃቀም

24.1. የፀረኤችአይ ቪ/ኤድስ ፈንድ ስራ ላይ የሚውለው በዚህ መመሪያ ለተጠቀሱት ድጋፎችና ከድጋፍ ጋር የተያያዙ ስራዎች ብቻ ይሆናል፡፡

24.2. የፈንዱ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በግብረኃይሉ ሰብሳቢ፣ የሂሳብ ክፍል ባለሙያ እና በሰራተኛ ማህበር ተወካይ ይሆናል፡፡

24.3. ከፈንዱ የባንክ ሂሳብ የሚወጣው በተራ ቁጥር

24.2 በተጠቀሱት የጣምራ ፊርማ ሆኖ ከሶስቱ በሁለቱ ገንዘብ ማውጣት ይቻላል፡፡

## 25. ስለ ድጋፍና እንክብካቤ

በኮርፖሬሽኑ የተቋቋመው ግብረኃይል እንደሁኔታው ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የድጋፍና እንክብካቤ በነጠላ ወይም በጣምራ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሀ. ወርሃዊ የገንዘብ ድጎማ

ለ. ለአንድ ጊዜ ወይም ለተከታታይ ወይም እንደ አመቺነቱ በየወቅቱ የሚደረግ የገንዘብ ወይም የቁሳቁስድ ጋፍ፤

ሐ. ዘላቂነት ያለው፣ የአንድ ጊዜ ማቋቋሚያ፣ በአይነት ወይም በገንዘብ ድጋፍ

መ. የምግብ፣ የአልባሳት፣ የህክምናድጋፍ

ሠ. የቤት ለቤት እንክብካቤና የምክር አገልግሎት ድጋፍ

ረ. የፀረኤች.አይቪ/ኤድስ ግብረ ኃይሉ እንደ ነገሩ አግባብነት በየጊዜው እያጠኑ የሚወስኑት ሌሎች የድጋፍና የእንክብካቤ አይነቶች፣

## 26. ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ሰራተኞች

በኮርፖሬሽኑ ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

26.1. ኤችአይ ቪ በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን ሰራተኞች፤

26.2. በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት (እድሚያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው) ፤

## 27. ድጋፍና እንክብካቤ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች

27.1. በዚህ መመሪያ ክፍል አንድ ተራ ቁጥር 2(2.2) በተገለፀው መሰረት ኤችአይ.ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለው ወይም የኤድስ ህመምተኛ ለሆኑ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረገው፡-

ሀ. ድጋፍና እንክብካቤ እንዲደረግለት ለጸረ ኤችአይ.ቪ. ግብረሀይል ጥያቄ ሲያቀርብና መረጃው ተቀባይነት ሲያገኝ፣

ለ. ሰራተኛው ኤችአይ ቪ/ኤድስ በደሙ ውስጥ ለመኖሩ ወይም የኤድስ ህመምተኛ ለመሆኑ ህጋዊ እውቅና ካለው የህክምና ተቋም የህክምና ማስረጃ ሲያቀርብ፣

ሐ. ሌላ የገቢ ምንጭ እንደሌለ ወይም ከሚያስተዳድረው ቤተሰብ አንጻር አነስተኛ የገቢ ምንጭ እንዳለው አግባብ ካለው አካል (ወረዳ፣ ፍ/ቤት) ከተረጋገጠ፣

27.2. ከወላጆቻቸው አንዱን ወይም ሁለቱን በኤች.አይ ቪ/ኤድስ ምክንያት በሞት ያጡ ህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ይሆናል፡፡

ሀ. ድጋፍና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ለጸረ ኤች.አይ.ቪ. ግብረኃይል በጽሁፍ ጥያቄ ሲቀርብ፣

ለ. ወላጆቻቸው ወይም ከወላጆቻቸው አንዱ ከኤች.አይ ቪ/ኤድስ ጋር በተያያዘ ህመም ምክንያት መሞቱን የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ሲቀርብ ወይም ኤች.አይ ቪ.በደሙ ውስጥ ያለመሆኑን ቀደም ሲል በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግብረኃይል በማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ፣

ሐ. በሞት የተለየው ወላጅ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኛ መሆኑሲ ረጋገጥ፣

መ. አመልካቹ ልጅ ስለመሆኑ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ግብረኃይል ተዘጋጅቶ በሰራተኛው ከተሞላው ቅጽ ጋር ተነፃጽሮ ወይም በሰው ሀብት አስተዳደር ከተሞላው ቅጽ ጋር ተመሳሳይ መረጃ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በነዚህ ቅጽ ካልተሞላ ስልጣን ካለው ፍርድ ቤት ህጋዊ የሞግዚትነት ማስረጃ ሲቀርብ፣

ሠ. ሌላ የገቢ ምንጭ እንደሌለ ወይም አነስተኛ የገቢ ምንጭ እንዳለው አግባብ ካለው አካል (ወረዳ፣ ፍ/ቤት) ከተረጋገጠ፣

27.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ2 መሰረት በአንደኛው ወላጃቸውን በኤች.አይ. ቪ/ኤድስ. ምክንያት በሞት ያጡ ህጻናት በመወከል ለጸረ ኤች.አይ. ቪ ግበረ ኃይል ወይም ለቅርንጫፍ/ፕሮጀክት ፎካል ፐርሰን ጥያቄ/በማመልከቻ ለማቅረብ የሚችለው ከሚከተሉት አንዱ ይሆናል፡፡

ሀ. በህይወት ያለው ወላጅ

ለ. ሁለቱም ወላጆቻቸው ከሌሉ የህጻኑ ወይም የህጻናቱ ሞግዚት

27.4. በዚህ አንቀጽ መሰረት ለሚደረገው የድጋፍና እንክብካቤ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፅ/ቤት ከሰው ሀብት አስተዳደር ጋር በመተባበር የሰራተኞችን እና 18 ዓመት ያልሞላቸውን ልጆቻቸውን ስም ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ቅጽ አዘጋጅቶ በእያንዳንዱ ሰራተኛ በሁለት ቅጂ እንዲሞላ አንዱ ለቅርንጫፍ/ ፕሮጀክት ፎካል ፐርሰን ሁለተኛው በሰው ሀብት አስተዳደር እንዲቀመጥና እንደ አስፈላጊነቱ ወቅታዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 28. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ

በዚህ መመሪያ መሰረት የኤችአይ ቪ/ኤድስ ታማሚ በመሆኑ ምክንያት ለሰራተኛው የሚደረግ የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ በሚከተለው ሥርዓት መሰረት ይፈጸማል፡፡

ሀ. ሰራተኛው የኤች.አይ ቪ/ኤድስ ታማሚ/በሽተኛ መሆኑ

ለ. ከኤችአይ ቪ ፈንድ የገንዘብ ድጋፍ የሚያስፈልገው መሆኑን በፅሁፍ በመግለጽ በዚህ አንቀጽ 27(1) (ለ) ላይ በተደነገገው መሰረት ቫይረሱ በደሙ መኖሩ ሥልጣን ካለው አካል የተሰጠ ህጋዊ ማስረጃ ሲያቀርብ፣

ሐ. ማንኛውምኤችአይ ቪ በደሙ የተገኘበት ሰው ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልገው መሆኑን በመግለጽ በፅሁፍ ሲያመለክት ወይም ሲረጋገጥ፣
በጸረ ኤች.አይ ቪ ግብረኃይል ውሳኔ ተገቢውን እንክብካቤና ድጋፍ ይደረግለታል፡

## 29. የኤድስ ፈንድ ዝውውርን በተመለከተ

29.1 የፈንድ እጥረት ዝዉዉር

በዚህ መመሪያ መሰረት የኤድስ ፈንድ ዝውውር ከዋና መ/ቤት ወደ ፕሮጀክት ወይም ከፕሮጀክትና ቅርንጫፎች ወደ ዋና መ/ቤት የሚደረገው በሚከተለው ሥርዓት ይሆናል፡፤

29.1.1 የፈንድ እጥረት የገጠመው ግብረሃይል ጉዳዩን አስመልክቶ ድጋፍ እንዲደረግለት የድጋፍና እንክብካቤ ስራውን ለሚያስተባብረው ለሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ በፅሁፍ ያሳውቃል፤

29.1.2. የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የቀረበለትን ጥያቄ ተገቢነት ያጠናል፤

29.1.3 መምሪያው የሌሎች ግብረ ሃይሎች የፋይናንስ አቅምና ፈንድ አጠቃቀምን በማየትና ከግብረሃይሎቹ ጋር በመነጋገር የፈነድ ዝውውር እንዲደረግ ያደርጋል፤

29.2 ፕሮጀክቶች ሲዘጉ ሊኖር የሚችል የፈንድ ዝዉዉር

29.2.1 የሚዘጋዉ ፕሮጀክት ሙሉ ለሙሉ አዲስ ፕሮጀክት ሲይዝ ንዑስ ኮሚቴዉ በአካዉንቱ ያለዉን ገንዘብ እንደያዘ ወደ አዲሱ ፕጀክት ይዛወራል ሂደቱን ለአብይ ኮሚቴ ያሳዉቃል፡፡

በሂደበት አካባቢ ተመሳሳይ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

29.2.2. የሚዘጋ ፕሮጀክት ተበትኖ ሠራተኞች ወደ ተለያዩ የሥራ ክፍል ከተዛወሩ በፕሮጀክት የነበረዉ ንዑስ ኮሚቴ የሂሳብ ደብተር ላይ የሚገኝ ገንዘብን በተመለከ ተኦዲት አስደርጎ ለሴ/ወ/ጉ/መምሪያ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

የሴ/ወ/ግ/መምሪያ አጣርቶ በጀቱ በዋና መ/ቤት በሚገኝ አብይ ኮሚቴ ሂሳብ እንዲዞር መረጃ በማደራጀት የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

አብይ ኮሚቴዉ የደረሰበትን የዉሳኔ ሀሳብ አጣርቶ ትእዛዝ ይሰጣል ፡፡

## 30. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ ስለማሳወቅ

የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ በሚከተለው አኳኋን ይፋ ይደረጋል፡-

30.1. መመሪያውን ለሰራተኞች በማሳወቅ፣

30.2. በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት ፣ዘርፍ ፣ቅርንጫፎችና ፕሮጀክቶች ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ፣

30.3. በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች በኩል ለሰራተኞች በማሳወቅ፣

## 31. የድጋፍና እንክብካቤ ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

ድጋፍና እንክብካቤ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ውስጥ ቢያንስ በአንዱ ምክንያት ሊቋረጥ ይችላል፡፡

31.1. ድጋፍና እንክብካቤ እንዲቋረጥ ሰራተኛው ወይም የህጻኑ ወላጅ ወይም ሞግዚትና አሳዳሪ በጽሁፍ ሲጠይቅ፣

31.2. ድጋፍና እንክብካቤውን ለመጀመር ምክንያት የነበረው የኢኮኖሚ ወይም የጤናና ሌላ ችግር የተወገደ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

31.3. ድጋፍና እንክብካቤ ሲደረግ የቆየው በሀሰት ማስረጃ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

31.4. ድጋፍና እንክብካቤ ሲያገኝ የቆየው ልጅ ኤች.አይ ቪ. በደሙ ውስጥ ባይኖርም 18 ዓመት ከሞላው፣

31.5. ከላይ በአንቀፅ31(4) የተጠበቀው እንዳለ ሆኖ እድሚያቸው 18 ዓመት የሞላቸው ልጆች የኮሌጅ ወይም የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ላይ ከሆኑ የግብረኃይሉን

በጀት እና የፋይናንስ አቅም ሊጎዳ የማይችል ከሆነ ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ በግብረኃይሉ ውሳኔ መሰረት ድጋፉ ሊቀጥል ይችላል፡፡

31.6. ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግለት ሰራተኛ ወይም ህጻን በሞት ሲለይ፣

31.7. የኮርፖሬሽኑ ኤችአይ ቪ/ኤድስ በጀት አቅም ድጋፍና እንክብካቤውን ለማስቀጠል የማያስችል ሲሆን፣

31.8. ድጋፍ የሚደረግለት ልጅ ወይም ልጆች ከመኖሪያ አካባቢው ርቀው ከድጋፉ በቀጥታ ተጠቃሚ ሊሆን የማይችልበት ሁኔታ ካለ ወይም ከሀገር ውጭ ከሆነ፣

## 32. ከኤች አይ ቪ ኤድስ ጋር የተያያዙ የዲሲፕሊን ጥፋቶች

በስራ ቦታዎች ኤች.አይ ቪ/ኤድስን ለመቆጣጠር እንዲቻል ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች መፈጸም በዲሲፕሊን ያስቀጣል፡፡

32.1. ኮርፖሬሽኑኤችአይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ሆን ብሎ ማወክ፣

32.2. በስራ ቦታዎች ወሲባዊ ጥቃት መፈጸም ወይም ለመፈፀም መሞከር

32.3. ሰራተኞች ወይም ስራ ፈላጊ አመልካቾች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ እንዲያደርጉ ወይም በነጻ ፍላጎታቸው ያደረጉትን የኤች.አይ ቪ የምርመራ ውጤት ይፋ እንዲያደርጉ ማስገደድ፣

32.4. በሥራ ምክንያት ያወቀውን የሰራተኞች የኤች.አይ.ቪ ምርመራ ውጤት ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ የህክምና መረጃ በስራው አስገዳጅነት ምክንያት መግለጽ ከሚገባው ውጭ ያለግለሰቡ የጽሁፍ ስምምነት ለሌላሰው ይፋ ማድረግ፣

32.5. ኤች አይ ቪ በደሙ ውስጥ በመኖሩ ወይም የኤድ ስህመምተኛ በመሆኑ ምክንያት በትምህርትና ሥልጠና፣ በደረጃ እድገት፣ በዝውውር፣ በድልድልና በስራ ዋስትና ወይም በሌላ ሥራ ሁኔታ ረገድ በማንኛውም ሰራተኛ አድልኦና ልዩነት መፈጸም፣

32.6. ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት በሥራ ቦታዎች ኤች.አይ. ቪ/ኤድስን ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚያስችል ድርጊቶችን መፈጸም፣

32.7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እስከ (6) ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ የሆነ አድሎአዊ አሰራር ወይም ህገወጥ ድርጊት መፈፀም፣

## 33. ስለ ዲሲፕሊን ክስ አቀራረብና ስለ ውሳኔ አሰጣጥ

33.1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈጸመበት ማንኛውም ሠራተኛ ለኮርፖሬሽኑ/ቅርንጫፎች /ፕሮጀክት የበላይ ሀላፊ በፅሁፍ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

33.2. የኮርፖሬሽኑ ቅርንጫፎች /ፕሮጀክት የበላይ ሀላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የቀረበለትን ጉዳይ ሊጣራ የሚገባ መሆኑን ሲያምንበት አቤቱታ በቀረበበት ሰራተኛ ስለ መፈጸሙ ተጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲቀርብ ለኮርፖሬሽኑ ቅርንጫፎች ፕሮጀክት ዲሲፕሊን ኮሚቴ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

## 34. ስለ ዲሲፕሊን ቅጣት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 32 ከተመለከቱት ጥፋቶች ቢያንስ አንዱን ፈጽሟል ተብሎ ክስ የቀረበበት ሰራተኛ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 377/96 በመስሪያ ቤቱ የዲሲፕሊን መመሪያ የተመለከቱት ከባድ ቅጣቶች መካከል አንዱን ይቀጣል፡፡

## 35. ከመመሪያው ጋር የሚቃረኑ ሕጎችና አሰራሮች

35.1. ይህ መመሪያ የፌደራል የመንግስት የልማት ድርጅቶች ኤጀን ሲባወጣው የልማት ድርጅቶች የሥራ ቦታዎች የኤች.አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ጋር የሚቃረን ወይም ክፍተት ያለው ሆኖ ሲገኝ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ ቦታዎች ኤች.አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መመሪያ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

35.2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ የሚቃረን መመሪያ፣ አሰራርና ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 36. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ የኮርፖሬሽኑ የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ፣ የኤችአይ ቪ ፎካል ፐርሰን እና የጸረ ኤች.አይ ቪ ግብረኃይል ለኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊ ሃሳብ በማቅረብ መመሪያው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻሻል ማድረግ ይቻላል፡፡

## 37. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ---------ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ዮናስ አያሌው (ኢንጂነር)**

**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ**